# ADDA BILISUMMAA OROMOO

OROMO LIBERATION FRONT | جبهة تحرير أورومـــو

Gaafa: 13-02-2013 تاريخ
Date:

Lakk.: 02/stm-abo/2013 رقم
No.:


## *የህዝበ ሙስሊሙን ፍትሃዊ ጥያቄ በሽፍጥና በማስፈራራት ለማፈን መፍጨርጨር ከባድ የፖለቲካ ኪሳራ ነው*

### *የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ*

የወያኔ መንግስት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ከኣንድ ኣመት በላይ በሰላማዊ መንገድ ብቻ እያቀረበ በሚገኘው ፍትሃዊ ጥያቄ ላይ ከማፌዝ ኣልፎ በጉልበት ኣስፈራርቶ የማፈን ጥረት መያያዙ እሙን ነው። በቅርቡ "*ጅሃዳዊ ሓረካት*" በሚል በሃሰት ተከውኖ የቀረበው ድራማውም የስርኣቱ የረጅም ጊዜ የማስፈራሪያና የኣፈና ተግባራት ኣካል መሆኑ ኣያጠያይቅም። ይህ መንግስት ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡና ምንም ኣይነት ትስስር የሌላቸውን የቪድዮ ምስሎች ኣቀነባብሮ የሙስሊሙን ማህበረሰብ ስም ለማጉደፍ ሲሞክር ይሄ የመጀመሪያው ኣይደለም። ወደ ስልጣን ከመጣበት ወቅት ኣንስቶ በታላቁ ኣንዋር መስጊድ እንዲሁም በሓረር፣ በጅማና በሌሎችም ከተሞች በሚገኙ መስጊዶች ተመሳሳይ የውንጀላ ሴራዎችን በመሸረብ የሃይማኖቱን ተከታዮች ኣስፈራርቶና ኣሸማቆ ዝም ለማሰኘት ሞክሯል። ምናልባት ይሄኛውን የተለየ የሚያደርገው ነገር ቢኖር "*መሪዎቻችንን ራሳችን እንምረጥ፣ መንግስት በሃይማኖታችን ጉዳይ ጣልቃ ኣይግባ*" የሚሉትን የማህበረሰቡ ጥያቄዎች ለማፈን ሲል ታሪክ የማይረሳውን ወንጀል እየፈመ መሆኑ ነው።

የህወሃት መንግስት የህዝብን ጥያቄ ለመቀልበስ ብሎ የሃሰት ድራማዎችን ኣቀነባብሮ ማቅረብ የተለመደ ተግባሩ ነው። ወደ ስልጣን ከመጣበት ወቅት ኣንስቶ ከዚህ ተግባር ኣልተቆጠበም። በተለይም የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን በሃሰት ወንጅሎ "ኣሸባሪ" ለማሰኘትና ይህንን ምኞቱንም ለኣለም ማህበረሰብ ለማሳመን እድሜውን ሙሉ ሲደክም ኖሯል። በሺዎች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ብሄርተኞችን በዚህ የሃሰት ውንጀላ ኣስሯል፣ ገድሏል፣ ለኣካል ጉድለት ዳርጓል፣ ቤት ንብረታቸውን ኣቃጥሏል፣ የተቀሩትንም ከሃገር ኣባሯል። በኣሰልቺ የመወንጀያ ድራማው ግን የትም ሊደርስ ኣልቻለም።

ከዚህም በተጨማሪ ከወራት በፊት ጆሃን ፐርሰን እና ማርቲን ሽቢዬ የተባሉትን ሁለት የስዊድን ጋዜጠኞች በኣሸባሪነት ወንጅሎ የፈለገውን ያህል ካሰራቸው በሁዋላ የለመደውን የስም ማጥፋት ድራማውን ከውኖባቸው የኣለም ማህበረሰብን ለማሳመን ሞክሮ ተዋረደ። ሁለቱ ጋዜጠኞች ከወያኔ እስር ቤት ተለቀው ሃገራቸው እንደገቡ የስርኣቱን ዋሾነት ለኣለም ማህበረሰብ ኣንዳጋለጡ ኣይዘነጋም።

ኣሁን በህዝበ ሙስሊሙ ላይ እየተሸረበ ያለው በሃሰት የመወንጀሉ ሴራም በተመሳሳይ መልኩ ለዘመናት ተከውኖ ያለውጤት ከቀረው ኣሰልቺ የመወንጀያ ድራማ ጋር ይመሳሰላል። ምናልባት ይሄኛውን ለየት የሚያደረገው ነገር ቢኖር ስርኣቱ እያደርገ ያለው የውንጀላ ጥቃት በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ሳይሆን ኣንድ ሰፊ ህዝብ በሚከተለው ሃይማኖት ላይ በሚያሳፍር መልኩ ያነጣጠረ መሆኑ ነው። የመንግስት እጅ በሃይማኖታችን ጉዳይ ጣልቃ ኣይግባ ያሉትን የሃይማኖት መሪዎች ወንጅሎ ለመምታት ሲባል ከቶ ሊመሳሰል በማይችል መልኩ ከኣለም ኣቀፍ ሽብርተኞች ጋር ኣቆራኞቶ ለማቅረብ ይህ ቀረሽ የማይባል ጥረት እየተደረገ ነው። በሰላማዊ መንገድ ብቻ ፍትሃዊ ጥያቄውን ያቀረበውን ህዝበ ሙስሊም በማስቀየምና በማበሳጨት ትእግስቱ

ተሚጦ ከሰላማዊ መንገድ ያፈነገጡ እርምጃዎችን ወደ መውሰድ እንዲገባ ለማድረግ ሆን ተብሎ ግፊት እየተደረገ ይገኛል።

የወያኔ መንግስት ኣስተዳድራለሁ በሚላቸው የሃገሪቷ ህዝቦች እንዲሁም በተለያዩ የሃይማኖት ማህበረሰቦች መካከል የማይጠፋ የግጭት እሳት እንዲለኮስ ይፈልጋል። ስርኣቱ የህዝብ ጥላቻ እየበረታበት በሄደና በዚህም ሳቢያ ከስልጣን መንበሩ ተገፍትሮ መውደቁ ኣይቀሬ መሆኑ በተቃረበ ልክ የማያባራ ግጭት በህዝቦችና በተለያዩ የሃይማኖት ማህበረሰባት መካከል ጭሮ ለራሱ ወደ መጣበት ለመመልስ ኣልያም በገዛ እጁ በጫረው የግጭት እሳት ኣጥፍቶ ለመጥፋት የተዘጋጀ ይመስላል። የኣንዱ ሃይማኖት ማህበረሰብ ከሌላኛው ሃይማኖት ማህበረሰብ ጋር በሰላምና በፍቅር ተከባብሮና ተደጋግፎ በጋራ እንዳይኖር በመካከላቸው የጥላቻና የጥርጣሬ መርዝ ይረጫል። የሃገሪቷ ብሄር ብሄረሰቦችም በመፈቃቀርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ መፃኢ የፖለቲካ እድላቸውን እንዳያቃኑ እርስ በራሳቸው ላይ ያነሳሳል። በጥቅሉ ወያኔ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ ኣይብቀል" ያለችውን እንስሳ ብሂል የሚከተል እጥፍቶ ጠፊ ቡድን መሆኑን በተግባራቱ እያረጋገጠ ይገኛል። ይህ ደግሞ ስርኣቱ ሃላፊነት የሚሰማው ህዝባዊ መንግስት ኣለመሆኑንና ለዘረፋ ኣላማው ብቻ በህዝብ ጫንቃ ላይ የተጣበቀ ሃይል መሆኑን በገሃድ ያስመሰክራል።

ማናቸውም የሃይማኖት ማህበረሰቦችና ብሄር ብሄረሰቦች ሁሉ በወያኔ መንግስት ኣጥፍቶ የመጥፋት ሴራ ላይ ነቅተው ሰይጣናዊ ጥረቱን በጋራ ለማክሸፍ መረባረብ የግድ ይሆናል። የማናቸውም ሃይማኖት ተከታይ ዜጋ ሁሉ ወያኔ ዛሬ በህዝበ ሙስሊሙ ላይ እየነዛ ባለው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ሳይታለል፣ ለመሆኑ ስርኣቱ በዚህ ወቅት እንዲህ ያለውን የውንጀላ ከበሮ የሚደልቀው ለምንድን ነው ብሎ ራሱን መጠየቅ ኣስፈላጊ ይሆናል። ወያኔ የተያያዘው ይህ ነጥሎ የመምታት ጥረት የተለመደ የከፋፍለህ ግዛ ስልቱ ኣካል መሆኑ ታውቆ በጋራ ርብርቦሽ መቀልበስ ይኖርበታል።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የወያኔ መንግስት ህዝበ ሙስሊሙ በተቀሩት የሃይማኖት ማህበረሰቦች ዘንድ እንዲጠላና በጥርጣሬ ኣይን እንዲታይ ለማድረግ የሚሸርበውን ያልተቋረጠ ከፋፋይ ሴራ በፅኑ ያወግዛል። እንዲህ ያለው ጠላታዊ ሴራ በማንኛውም ሃይማኖት ማህበረሰብ ላይ እንዲፈጸምም ኦነግ ኣይፈቅድም። የማንኛውም ሃይማኖት ማህበረሰብ መሪዎቹን ራሱ እንዲመርጥ፣ በሃሰት ውንጀላ የታሰሩት የህዝበ ሙስሊሙ ኣመራር ኣባላትም ኣንዲፈቱ ይጠይቃል። ኦነግ ሁሉንም ሃይማኖቶች በእኩልነት የሚመለከት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ኣንድን ሃይማኖት በሃሰት ወንጅሎ ወደ ጎን ለመግፋት የሚሸረበውን ሴራ በዝምታ መመልከት ኣይችልም። የተለያዩ ሃይማኖቶች ምእመናን ሃይማኖቶቻቸውን ኣቻችለው ለረጅም ዘመናት በፍቅርና በመተሳሳብ ኣብረው እንደኖሩት ሁሉ ለወደፊቱም ለስርኣቱ ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳ ሳይታለሉ ይህንን መልካም የኣብሮነት ባህላቸውን እንዲንከባከቡ የኦነግ ፍላጎት ነው። ኣለም ኣቀፉ ማህበረሰብና መንግስታትም እንዲህ ያለውን የወያኔ መንግስት ኣደገኛና ኣሰልቺ የውንጀላ ተግባር እያዩና እየሰሙ ዝምታ መምረጣቸው ስርኣቱ ይበልጥ የልብ ልብ ተሰምቶት ለከፋ እርምጃ እንዲዘጋጅ እያበረታታው ስለሆነ የውግዘት ድምፃቸውን በጊዜ ኣንዲያሰሙ እንጠይቃለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር

የካቲት 13, 2013